በ2016 በጀት ዓመት የተከናወኑ የፋይናንስና ህጋዊነት ሪፖርት፤

የአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ-መንግስት አንቀጽ 116(2) እና የዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራትን መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀጽ 10(2) ለመ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ዋና ኦዲተሩ ለተከበረው ም/ቤት የተከናወኑ ተግበራትን የሚገልጽ ሪፖርት እንደሚያቀርብ በተደነገገው መሰረት አስቻይ ሁኔታዎችን በመጠቀም በ2016 በጀት ዓመት የተከናወኑ የፋይናንስና ህጋዊነት ሥራዎች፣ የኦዲት ግኝቶችንና የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦችን የሚያሳይ የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል:-

በ2016 በጀት ዓመት በመደበኛና በልዩ ኦዲት የተከናወኑ የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቶች በሚመለከት

1. መ/ቤቱ በዚህ ሪፖርት ያካተተው የ218 መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፣በኦዲት ሂደት ወቅት እርምጃ የተወሰደባቸው ግኝቶች እና ያለፉት ዓመታት የኦዲት ውጤቶች እርምጃ አወሳሰድ የክትትል ኦዲት ሪፖርት ውጤት ነው፡፡ የ375 መ/ቤቶችን ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ የ218 (58.13%) መ/ቤቶች የኦዲት ሥራ ተከናውኗል፡፡ ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በአወቃቀር እርከን ሲታይ በክልል/ማዕከል 75(34.4%)፣በዞን 10(4.59%)፤በከተማ አስተዳደሮች 66(30.28%) ቀሪዎች 67(30.73%) በወረዳ ደረጃ ያሉ ናቸው፡፡
2. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶች፣ የሂሳብ መግለጫዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ሰራተኞች እና ኃላፊዎች የሰጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከ3ኛ ወገኖች የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች ሥራ ላይ ውለዋል፡፡
3. ከኦዲት ስልት አንፃር ኦዲቱ በንሞና እና በዝርዝር የኦዲት ስልቶች የተከናወነ ሲሆን ከ218 መ/ቤቶች ውስጥ 202(92.66%) በንሞና እንዲሁም 16(7.34%) መ/ቤቶች የልዩ ኦዲት ይሰራልን ጥያቄ በመቅረቡ በዝርዝር ኦዲት የተከናወኑ ናቸው፡፡

የኦዲት አስተያየትን በሚመለከት

4. ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ እና የኦዲት አስተያየት ከተሰጠባቸው 133 መ/ቤቶች ውስጥ **ለ35(26.32%) ንፁህ፣ ለ87 (65.41%) ለሚሆኑት ከዚህ በስተቀር** ፣ለ7(5.26%) **አጥጋቢ አይደለም**፣ለ4(3.01%) **አስተተያየት መስጠት አለመቻል** ፤ የሚሉ የኦዲት አስተያየት አግኝተዋል፡፡
5. ከላይ የከፋ የኦዲት አስተያየት ከተሰጣቸው መሃል ሂሳባቸውን ኦዲት አድርጎ የሙ-ያ አስተያየት ለመስጠት ቢቻልም መንግስት የመደበላቸውን ሀብት/ገንዘብ በአግባቡና ህጉ በሚፈቅደው አሰራር መሠረት ስራ ላይ ያላዋሉ፤ ሒሳባቸው የጎላ ችግር ስላለበት **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መ/ቤቶች አብክመ ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ኮሚሽን፣አብክመ ውሃና ኢነርጅ ቢሮ (የጠጣራ ሃብት ሚዛን መሳት ነበር ማስተካከያ እርምጃ ወስዷል፣ አብክመ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፣ፈለገ ህይወት አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣አብክመ መንገድ ቢሮ፣ ቦሩሜዳ ጠቅላላ ሆስፒታል እና ቃሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል (በተደረገው ውይይት ምልሽ ሰጥቷል ክትትል ተደርጎበት በሚቀጥለው ሪፖርት የምንገልጽ ይሆናል) ናቸው፡፡
6. በሌላ መልኩ የገንዘብ አያያዝና አስተዳደሩም ሆነ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን መርምሮ ተዓማኒና በቂ የሂሳብ አያያዝና አስተዳደር መኖሩን ለማረጋገጥና የሙ-ያ አስተያየት ለመስጠት ያላስቻሉ ጉልህና መሰረታዊ ችግር የተገኘባቸው በመሆኑ **"አስተያየት መስጠት አልተቻለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መ/ቤቶች፡- በአብክመ ወጣቶች ስፖርት ቢሮ የስፖርት ምክር ቤት ሂሳብ ፣አብክመ ግብርና ቢሮ (ምላሽ ሰጥቷል ክትትል ተደርጎ በሚቀጥለው ጥንቅር የምናካትት ይሆናል)፣በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር የሃን ጤና አጠባበቅ ጣቢያ እና ኮምቦልቻ ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት ናቸው፡፡

የኦዲት ሪፖርቶች ምላሽ አሰጣጥ በሚመለከት

7. በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 202 መ/ቤቶች መካከል መልስ ያልሰጡት 84(41.58%) መ/ቤቶች ሲሆኑ እነሱም የክልል /ማዕከል መ/ቤቶች 17፣ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር 1፣ ምዕራብ ጎጃም ዞን አስተዳደር 2፣ ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር 3፣ ማዕከላዊ ጎንደር ዞን አስተዳደር 5፣ ሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር 2፣ ኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን 3፣ ሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር 5፣ አዊ ብሄረሰብ ዞን አስተዳደር 1፣ ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር 27 እና ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር 18 ናቸው፡፡ በ2016 በጀት ዓመት ኦዲት ምላሽ የሰጡ መ/ቤቶች

ካለፈዉ በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር እየቀነሰ የመጣ ሲሆን የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና ተጠያቂነት ሥርዓት ከማጠናከር አኳያ ሰፊ ስራ መሰራት እንዳለበት ያሳያል፡፡

8. በልዩ ኦዲት የተሰሩት 16 መ/ቤቶችን በሚመለከት ጉዳዩ በክስ ሂደት ላይ እንደሆነ የፍትሕ አካላት በላኩት ግብረ-መልስ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ውጤትን በሚመለከት

9. በ2016 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ4 መ/ቤቶች ብር 1,879,676.78 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡ የኦዲት ሪፖርቱም ለሚመለከታቸው የፍትህ አካላት የተላከ ሲሆን ጉዳዩ በክስ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

የገቢ ሂሳብ ኦዲት ውጤት

10. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በአንድ መ/ቤት ገቢ ሲሰበስቡ በበራሪው የተሰበሰበውን የገንዘብ መጠን በቀሪው የገቢ ደረሰኝ ቅጠል ዝቅ አድርጎ በማስፈር ብር 376,787.09 ለግል ጥቅም ውሎ የተገኘ ሲሆን የኦዲት ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ተልኳል፡፡ ጉዳዩም በክስ ሂደት ላይ እንደሆነ የፍትህ አካላት በሪፖርት አሳውቀውናል፡፡

ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ

11. የተጨማሪ እሴት ታክስን አስመልክቶ በወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ማንኛውም በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ደረጃ የሚገኝ ድርጅት በከፋይነት ተመዝግቦ እቃ/አገልግሎት ሲያቀርብ ለክፍያው የቫት ደረሰኝ/ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ያለበት እና ግዥ የሚፈጽሙ አካላትም ማስረጃው እንዲቀርብላቸው የማድረግ ሃላፊነት የተጣለባቸው ቢሆንም የደሴ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የተሽከርካሪ ጎማ ግዥ ሲፈጸም ለመንግስት ገቢ ያልሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 159,999.99 ተገኝቷል፡፡

    በመሆኑም ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ በመሆኑ አቅራቢው ታክሱን ለገቢ ሰብሳቢው አካል ገቢ አድርጎ ማስረጃ እንዲያቀርብ መደረግ እንዳለበት ለሚመለከታቸው የፍትህ አካላት አሳስበናል፡፡

ያልተሰበሰበ (በውዝፍ የሚገኝ)ገቢ፤

12. በ2016 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ 218 መ/ቤቶች ውስጥ በ43 መ/ቤቶች ብር 47,278,208.55 ባለው የገቢ አሰባሰብ ስርዓት መሰረት ገቢው በወቅቱ ሳይሰበሰብ በውዝፍነት ተገኝቷል፡፡ ከፍተኛ ያልተሰበሰበ የመንግስት ገንዘብ ከሚታይባቸው ዞኖች መካከል ደቡብ ወሎ አስተዳደር ብር 24,785,004.58 (52.42%) እና አሮሞ ብሔረሰብ ዞን አስተዳደር ብር 12,836,249.67 (27.15%) ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ::

ያልተሰበሰበ ገቢ ተብሎ ከተያዘው ገንዘብ ዉስጥ በ1 መ/ቤት ብር 1,852,891.52 (3.92%) የተሰበሰበ መሆኑ የተገለፀልን ሲሆን ቀሪው ብር 45,425,317.03 (96.08%) በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ይህ የጥንቅር ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ድረስ ስለመሰብሰቡ ግብረ-መልስ አልተሰጠም፡፡

ያልተሰበሰበ 2% የንግድ ስራ ትርፍ ግብር፤

13. በገቢ ግብር አዋጅና ደንብ እንደተመለከተው ከተወሰነ መጠን በላይ የሆነ የእቃ ግዥና የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጸም ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ መሰሠብሰብ የሚገባው 2% የንግድ ስራ ትርፍ ግብር በ7 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 109,468.79 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

ገቢው ከየሚመለከታቸው ላይ ክትትል ተደርጎ እንዲሰበሰብ በየሪፖርቶቹ ባሳሰብነው መሰረት መሰብሰቡን የሚገልጽ ማስረጃ በግብረ መልስ ያልተገለፀ በመሆኑ ያልተሰበሰበው የንግድ ስራ ትርፍ ግብር በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች

14. ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ36 (16.51%) መ/ቤቶች ብር 22,123,741.07 የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት በኦዲት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የገቢ ደረሰኞችን ለኦዲት ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከል ከፍተኛውን ድርሻ የያዙና ከብር 200,000 በላይ ከሆኑት መካከል፡- ቦሩ ሜዳ ጠቅላላ ሆስፒታል ብር 7,214,170.86 የተሰበሰበባቸው፣አልቡኮ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 5,463,882.48 የተሰበሰበባቸው፣ ተሁለደሬ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 2,705,546.80 የተሰበሰበባቸው፤የመካነ እየሱስ ከተማ አስተዳደር ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ስጪ ማዕከል ብር 1,214,847.24 የተሰበሰበባቸው፤

አንጎለላና ጠራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 715,206.45 የተሰበሰበባቸው፣የጎንጅ ቆለላ ወረዳ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ስጪ ማዕከል ብር 709,235.00 የተሰበሰበባቸው፤ደብረ ብርሃን አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 660,465.80 የተሰበሰበባቸው፣ባቲ ወረዳ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማእከል ብር 555,848.08 የያዙ የመደበኛ ሂሳብ የገቢ ማጠቃለያ ደረሰኞች፣ የኪንፋዝ ወረዳ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ስጪ ማዕከል ብር 437,580.00 የያዙ የተሰበሰበባቸው፤ቃሉ ወረዳ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጭ ማዕከል ብር 352,801.22 የተሰበሰበባቸው፣ ሲያደብርና ዋዩ ወረዳ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ስጪ ማዕከል ብር 349,035.82 የተሰበሰበባቸው፣ተሁለደሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ብር 215,291.23 የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ስራ ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኘነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

ይህም ለኦዲት ስራ ባልቀረቡት ደረሰኞች ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ በኦዲት ባለመረጋገጡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ገደብ የተጣለበትና ማጭበርበር ድርጊት ይፈጸምባቸው ወይም አይፈጸምባቸው ጥርጣሬን ያሳደረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች የገቢው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ እና ማስተካከያ/እርምጃ እንዲወሰድ ባሳሰብነው መሰረት በአንድ መ/ቤት ብር 1,214,847.24(5.49%) የያዘ ደረሰኝ ቀርቦ የተረጋገጠ ሲሆን በቀሪው ብር 20,908,893.83 (94.51%) ላይ የተረጋገጠና የተወሰደ እርምጃ እስከዚህ ሪፖርት ጥንቅር ድረስ አልተገለፀም፡፡

የተሰብሳቢ ሂሣብ ኦዲት ውጤት

በወቅቱ ያልተሰበሰበ (ያልተወገደ) ተሰብሳቢ ሂሣብ

15. ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ68 መ/ቤቶች ብር 2,811,923,438.27 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ተሰብሳቢ ሂሳቡ ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመሰብሰቢያ ወይም ከመዝገብ የመሰረዣ ጊዜ እንዳላቸው ከገንዘብ ቢሮ በቁጥር 6/2004 በክፍል-4 በተላለፈው መመሪያ የተገለጸ ቢሆንም አብዛኞቹ መ/ቤቶች ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ጊዜው በዘገየ ቁጥር ያለመሰብሰብ ዕድሉ እየሠፋ ስለሚሄድ መመሪያው በሚያዘው መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርቶቻችን ገልጸናል፡፡

ይህም መ/ቤቶቹ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ በሪፖርት ባሳሰብነው መሰረት ብር 1,326,621.02(0.05%) የተሰበሰበ ሲሆን ቀሪው ብር 2,810,596,817.25 (99.95%) ይህ ዘገባ ጥንቅር እስከተሰራበት ድረስ ተሰብሳቢ ሂሳቡ ስላለበት ደረጃ አልተገለፀም፡፡

16. በሌላ በኩል የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነት እንዳስፈላጊነቱ በሚመለከተው 3ኛ ወገን ማረጋገጫ እንዲቀርብለት የሚደረግ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ስለትክክለኛነቱ ከ3ኛ ወገን (ከሚሰበሰብባቸው አካላት) ለማረጋገጥ ከተጠየቀው የተሰብሳቢ ሂሳብ መካከል በ6 መ/ቤቶች ብር 91,026,381.49 የ3ኛ ወገን ማረጋገጫ አልቀረበለትም፡፡

ከእነዚህ ተሰብሳቢ ሂሣቦች ከብር 3 ሚሊዮን በላይ ድርሻ ካላቸው መካከል የደቡብ ወሎ ዞን ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 28,961,632.18፣ደሴ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 24,323,688.59፤ቃሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 16,052,707.62፣ደሴ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 14,525,002.67፣ቦሩ ሜዳ ጠቅላላ ሆስፒታል ብር 3,675,134.86፣ ኩታበር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 3,102,912.98 የሦስተኛ ወገን ማረጋገጫ ያልተገኘላቸውን ተሰብሳቢ ሂሳብ በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡

ይህም ሂሳብ ትክክለኛ ተሰብሳቢና ባለቤት ያለው ስለመሆኑ በማረጋገጥ መ/ቤቶቹ ተሰብሳቢው ሂሳብ የተያዘበትን አግባብ በማጣራት በሚገኘው ውጤት መሠረት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ በሪፖርት ያስገነዘብን ቢሆንም የተወሰደውን እርምጃ አስመልክቶ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት ተሰብሳቢ ሂሣብ

17. የ2015 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ13 መ/ቤቶች ብር 11,824,743.03 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር (ከማን እደሚሰበሰብ የሚያሳይ ዝርዝር) ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡
ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተሰብሳቢ ሂሣብ በተመለከተ ገንዘቡ ከማን እንደሚፈለግ ገላጭ ባለመሆኑና በጥቅሉ ስለተመዘገበ ባለቤቱን አውቆ ከሚመለከተው ላይ ለመሰብሰብ ወይም ከመዝገብ ለመሰረዝ የማያስችል በመሆኑ ተሰብሳቢ ሂሳቡ በየስሙ ተለይቶ የተቀፅላ ሌጀር ሊዘጋጅለትና ክትትል እየተደረገ ሊሰበሰብ/ከመዝገብ ሊሰረዝ/ እንደሚገባው በሪፖርታችን ብናሳስብም ይህ የጥንቅር ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ድረስ የተሰጠ ግብረ መልስ ባለመኖሩ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ማወቅ አልተቻለም፡፡

የወጪ ሂሳብ ኦዲት ውጤት፤

የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ እና ዘዴዎች

18. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መካከል በ2 መ/ቤቶች ብር 3,175,556.21 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ ሪፖርቱን ለፍትህ አካላት ያሳወቅን ሲሆን ጉዳዩ በክስ ሂደት ላይ እንዳለ አሳውቀውናል፡፡

ለሚመለከተዉ ፈሠስ ሳይደረግ የቀረ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

19. በከሚሴ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ለስራ ተቋራጮች የተከፈለና በተቋራጮች በኩል መከፈል የነበረበት የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 202,186.23 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡
ገንዘቡ በወቅቱ ፈሠስ መደረጉ ክትትል ባለመደረጉ ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ተሰብስቦ ለረዥም ጊዜ በሰብሳቢዎቹ (ስራ ተቋራጮች) እጅ እየተያዘ ለስራ ማስኬጃ የሚውልበትና ከጊዜ ብዛትም ፈሰስ የማይደረግበት ሁኔታ በመኖሩ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ፈሰስ መደረጉ በወቅቱ ሊረጋገጥ ይገባዋል፡፡

አላግባብ የተፈፀመ ክፍያ፤

20. ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ107 መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም ሌሎች ክፍያዎች

በድምሩ ብር 19,643,705.44 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ አላግባብ ከተከፈለው ክፍያ ዋና ዋናዎቹን ለመጠቀስ፡-

- የአብክመ ትምህርት ቢሮ ብር 1,727,755.38 ሲሆን ይህም ቢሮው በደቡብ ሜጫ ወረዳ የዳኔ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ የ2ኛ ዙር ክፍያ ሲፈጸም በብልጫ የተከፈለ እና በምዕራብ ጎጃም ዞን ደንበጫ ዙሪያ ወረዳ የአንጀኔ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የቤተ-ሙከራ ህንጻ ግንባታ ለማከናወን በወጣው ጨረታ መሰረት ተወዳድረው አሸናፊ ከሆኑት ከየኒላው ተማረ እና ጓደኞቻቸው ጠ/ስራ ተቋራጪ ህ/ስ/ማሕበር ጋር ውል ተይዞ ክፍያ ሲፈጸም ባልተሰራ ስራ አላግባብ የተከፈለ እና ሊሎች ክፍያዎች፣
- ቃሉ ወረዳ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ብር 279,204.12 ሲሆን ይህም የጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ዋን ዋሽ ፕሮጀክት ሂሳብ የቦሰና ጤና አጠባበቅ ጣቢያ መጸዳጃ ቤት ግንባታ ለማሰራት ከአንድ ጠቅላላ ስራ ተቋራጪ ጋር ውል ተወስዶ ግንባታ የተጀመረ ሲሆን ተቋራጩ በውለታው መሰረት ስራውን ሳያጠናቅቅ ያቋረጠ በመሆኑ ቅድሚያ ክፍያ ተወስዶ ያልተመለሰ፤አላግባብ በድጋሜና በብልጫ የተከፈለ ውሎ አበል እና የነዳጅ ሂሳብ፣
- ቦረና ወረዳ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ብር 741,614.89 ባልተፈቀደ በጀት ላይ የተፈፀመ የመስተንግዶ ክፍያ፣ ስራ ላልተሰራበት የተፈጸመ የደመወዝ ክፍያ እና በተመሳሳይ ቀን በድጋሚ እና ከታሪፍ በላይ የተከፈለ ውሎ አበል ክፍያ፣
- ሐይቅ ከተማ አስተዳደር ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ብር 1,095,830.00 የሐይቅ ከተማ አስተዳደር ከተማና መሰረተ ልማት ጽ/ቤት የከተማ መሬት ቆጠራ ፋይል ማደራጀት ስራ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሳይሰራና ሳይጠናነቅቅ ስራው እንደተሰራ ተደርጎ የተከፈለ ሂሳብ፣
- ዳዋጨፋ ወረዳ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ብር 383,920.49 በብልጫ የተከፈለ የግንባታ ክፍያ፣ በታሪፉ መሰረት ያልተከፈለ እና በተመሳሳይ ቀን በድጋሜ የተከፈለ ውሎ አበል፣
- ባቲ ከተማ አስተዳደር ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ብር 265,589.00 ባልተፈቀደ በጀት የተፈጸመ የመስተንግዶ ክፍያ፣የግለሰቡን ማንነት የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖርና ስራው ስለመሰራቱ ማረጋገጫ ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ እና በተመሳሳይ ቀን በድጋሜ የተከፈለ ውሎ አበል፣

- የባቲ ወረዳ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ብር 476,168.00 በብልጫ የፀደቀ ወጪ፣በተመሳሳይ ቀን በድጋሜ የተከፈለ ውሎ አበል፣ከበጀት ዓመቱ ውጪ የተከፈለ፣ ከመመሪያ ውጭ የተፈፀመ የተንቀሳቃሽ ዋይፋይ ግዥ የሚሉት ናቸው፡፡

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት አካላት የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና መጠየቅ ያለባቸውም እንዲጠየቁ ባሳሰብነው መሰረት ይህ ሪፖርት እስተጠናቀቀበት ድረስ ብር 321,180.35 የተመለሰ ሲሆን ቀሪው ብር 19,322,213.09 በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አልተገለፀልንም፡፡

መመሪያን ያልተከተለ የግንባታ ስራዎች ወጪን በተመለከተ፤

21. ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ አፈፃፀም መመሪያን ባልተከተለ መንገድ በ12 (5.50%) መ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,390,125.07 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-
    - በኪንፋዝ በገላ ወረዳ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል፡- ጤና ጽ/ቤት በዋን ዋሽ ፕሮጀክት ሂሳብ የጭቅቂ ቀበሌ የመፀዳጃ ቤት ግንባታ ለተከናወነበት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈጸም እና የኢንሱሌተር ግንባታዎች ሲከናወኑ፤ በጨጨሆ ቀበሌ የእጅ ውሃ ጉድጓድ ግንባታ ስራ፤በሮቢት ቀበሌ የመፀዳጃ ቤት ግንባታ፤የአብዚ ቀበሌ የመፀዳጃ ቤት ግንባታ እና ወርቄ ቀበሌ ቡአከዚት ጎጥ የእጅ ውሃ ጉድጓድ ግንባታ ክፍያ ሲፈጸም የግንባታ ስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ እና በስላሬ ከተማ ከተገነቡ ዲቾች ውስጥ የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈጸም ጊዜያዊ ርክክብ ሳይቀርብ የተፈጸመ ብር 1,093,492.61፣
    - የዳባት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል በወረዳው ጤና ጽ/ቤት በዋን ዋሽ ፕሮጀክት በታላቅ-መስክ ቀበሌ ፕላሲንታ ቲት ግንባታ የመጀመሪያ ዙር ክፍያ ፤የዴንሳ አምባ ቀበሌ የጤና ኬላ መፀዳጃ ቤት ግንባታ የመጀመሪያና የመጨረሻ ዙር ክፍያ እና የደቋ ቀበሌ የንጹህ መጠጥ ውሃ ግንባታ የመጀመሪያ ዙር ክፍያ ሲፈጸም የግንባታ ስራ ስፍር ልኬት ሳይቀርብለት የተከፈለ ብር 789,749.95፣
    - የሰከላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል የጎለም ጤና ጣቢያ የደረጃ ማሳደግ ግንባታ ስራ ሶስተኛ ዙር ክፍያ ሲፈጸም የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 108,858.72፣

- የጭልጋ ወረዳ ቁጥር-2 ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል የወረዳው ጤና ጽ/ቤት በኳክ ጤና ኬላ መፀዳጃ ቤት ለመገንባት ከአንድ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ጋር ውል ይዞ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን የመጀመሪያ ዙር ክፍያ ሲፈጸም ስራው በትክክል ለመሰራቱ የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸም ክፍያ ብር 173,157.25፣
- የሰሜን ወሎ ዞን ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል፡- የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በግቢው ውስጥ የላብራቶሪ ምርመራ የሚያሰሩ ታካሚዎች ማረፊያና የራጅ ምርመራ የሚያደርጉ ህሙማን ማረፊያ ግንባታ ክፍያ ሲከፈል የግንባታ ስራ ዝርዝር ሳይቀርብ የተከፈለ ሂሳብ ብር 517,937.86፤
- ቃሉ ወረዳ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል፡-የቃሉ ወረዳ መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ጽ/ቤት በ015 ቀበሌ ስሙ ቱሉባቡኛ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ላይ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ግንባታ ስራ በአገረሰን ኢንጅነሪንግ የውሃ ጉድጓድ ስራ ተቋራጭ ተከናውኖ ክፍያ ሲፈጸም ያለተጨማሪ ውልና የስራ ስፍር ልኬት ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 314,014.30፣ናቸው፡፡

ስለሆነም ስራው ስለመከናወኑ የሚያሳዩ የስራ ዝርዝር፣የስራ ልኬት ወረቀት እና ጊዜአዊ ርክክብ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈፃሞ የተገኘባቸው ሲሆኑ ሥራው በትክክል በስራ ዝርዝሩ መሰረት ስለመሠራቱ በገለልተኛ የምህንድስና ባለሙያ እንዲረጋገጥ ሆኖ ያልተሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ ገንዘቡ ከሚመለከታቸው አካላት ተመላሽ እንዲደረግ እና ድርጊቱን የፈጸሙት አካላት ተጠያቂ እንዲሆኑ በኦዲት ሪፖርቶች ያሳሰበን ቢሆንም ይህ ጥንቅር እስከተጠናቀቀበት ድረስ የተወሰዱ ማስተካከያ/እርምጃ የሚገልጽ ሪፖርት አልደረሰንም፡፡

ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ፤

22. ማንኛውም ክፍያ ተፈጽሞ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ሲገባው ይህን በመተላለፍ በ19(8.72%) መ/ቤቶች የተለያዩ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር 45,119,991.65 ህጋዊ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞና በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

    በአጠቃላይ ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ ካለፈው ዓመት ብር 7,939,701.65 ጋር ሲነፃፀር ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በቁጥር በአንድ የቀነሰ ሲሆን በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 37,180,290.00 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ ይህም በኦዲት ማስረጃ አቀራረብ ዙሪያ ችግሩ እየጨመረ መምጣቱን ያመላክታል፡፡ ከእነዚህም መካከል ደሴ ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

ብር 21,299,343.29፣አብክመ አደጋ መከላከል ምግብ ዋስትና ኮሚሽን ብር 15,000,000,00፣ከሚሴ ከተማ አስ/ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 2,958,094.40 ፣አብክመ ጤና ቢሮ ብር 2,904,531.58 እና ስከላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 1,816,766.00 በኦዲት በማስረጃ አቀራረብ ዙሪያ ችግሩ ገዝፎ ከብር አንድ ሚሊን በላይ የታየባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡

23. ስለሆነም ክፍያውን የፈፀሙት መ/ቤቶች ለእያንዳንዱ ክፍያ በከፈሉት ገንዘብ ልክ ተገቢውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ማግኘታቸውን የሚያመላክት ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ እንዲያያዝ ወይም ያለማስረጃ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከተው አካል ላይ ተመላሽ እንዲሆን ለየመ/ቤቶች በፃፍነው ሪፖርት የገለጽን ቢሆንም ይህ ጥንቅር እስከ ተጠናቀቀበት ድረስ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ የተወሰደው እርምጃ አልተገለፀልንም፡፡

ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ የወጪ ማስረጃዎች

24. ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመባቸው ዕቃና አገልግሎቶች በትክክል ስለመዋላቸው ለማረጋገጥ የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ8 (3.67%) መ/ቤቶች ብር 76,576,307.50 የያዙ የወጪ ማስረጃዎች ሊቀርቡ ያልቻሉ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ከብር 900,000.00 በላይ ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡- ጉባላፍቶ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 35,570,960.22፣ራያ ቆቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 24,208,478.04፣ ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 7,899,427.11፣አብክመ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪና ማሽን ቴክኖሎጅ ልማት ኢንተርፕራይዝ ብር 6,526,307.71፣ቃሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 1,299,447.89 እና መቅደላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 911,100.93 ዋና ዋናወቹ ናቸው፡፡

    ስለሆነም ማስረጃዎቹ ተገቢ ክፍያ እንደተፈፀመባቸውና እነዳልተፈጸመባቸው ብሎም ለማጭበርበር ወንጀል አለመዋላቸው ባለመረጋገጡ ስጋት ያስከተለ በመሆኑ የወጪው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ በተጨማሪም ሰነዶቹን ማቅረብ የነበረባቸው/የሰወሩ ሠራተኞች ተጠያቂ እንዲሆኑ በኦዲት ሪፖርቶቻችን ለየተቋማቱ ያሳወቅን ቢሆንም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ ይህ ሪፖርት እስኪጠናከርበት ጊዜ ባለመምጣቱ ግኝቱ ያለበትን ሁኔታ ማወቅ አልተቻለም፡፡

የግዥ ስርዓትን ያልተከተለ የወጪ ሂሳብ ፤

25. የዕቃና አገልግሎት ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለው የግዥ መመሪያ መሰረት ስለመፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና የዋጋ ቅናሽ ለመገኘቱ እና የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች የተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ46 (21.10%) መ/ቤቶች ብር 103,086,246.50 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ አፈፃፀም ስርዓት የሚጠይቀውን መስፈርት ሳያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡ የግዥ አፈጻፀም ችግሮች ጎልቶ የታየባቸው ከብር 1,000,000.00 በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

- አብክመ ትምህርት ቢሮ ብር 24,672,000.00 ለፈተና አገልግሎት የሚውል 240 ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተር ለመግዛት በወጣው ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ መሰረት ከተወዳደሩት 8(ስምንት) ተወዳዳሪዎች መካከል ዝቅተኛ ዋጋ በማቅረብ አሸናፊ የሆኑት ድርጅት በጨረታ ለመሳተፍ የሚያበቃቸውን የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ከባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች መምሪያ በቁጥር ደ/አገ/4543/2015 በቀን 08/03/2015 ተሰጥቷቸው እያለ ግለሰቡ /ግብር ከፋይ ነጋዴው/ ሰነድ ስርዝ ድልዝ በማድረግ በቀን 08/08/2015 ዓ.ም እንደተሰጣቸው አድርገው ያቀረቡ እና በጨረታ ሂደቱ አሸናፊ ተደርገው የተመረጡ በመሆናቸው ከግዥ መመሪያ ውጪ የተፈጸመ ግዥ፣
- አብክመ መሬት ቢሮ ብር 17,889,173.17 ለመስክ ካርታ ህትመት የሚውል ወረቀት የፕሪተር ቀለም፣የፕሎተር ቀለም በሴት፣የጽ/መሳሪያ እና የቴምሴት ህትመት እቃዎች፣ የማሳ ካርታ ህትመት እና ለተሽከርካሪዎች የተለያዩ የጥገና አገልግሎቶች ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈፀም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ባልቀረበበት ሁኔታ በፕሮፎርማና በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ ግዥ፣
- አብክመ ርዕሰ-መስተዳድር ጽ/ቤት ብር 8,595,011.01 የአዳራሽ ጥገና ስራ ሲከናወን በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈፀም ሲገባው ያለምንም አሳማኝ ምክንያት በቀጥታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ፣
- ደሴ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 4,839,267.48 የሆስፒታሉ የመድሃኒት ፣ የግንባታ፣የአላቂ ዕቃ፣ የተለያዩ ዕቃዎች ግዥ፣የኤሌክትሮኒክስ ዕቃ፣የጽዳት ዕቃዎች፣ የጽህፈት መሳሪያዎች፣የህንጻ መሳሪያ ግዥ ከመፈጸሙ በፊት የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት እና የነዳጅ ግዥ ለጀኔሬተሮች ሲፈጸም የግዥ መጠየቂያ ሳይቀርብ የተፈፀመ፣

- ወይዘሮ ስህን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ብር 4,812,503.99 ለትምህርትና ስልጠና አገልግሎት የሚውል የጽህፈት መሳሪያና ኮምፒውተር ዕቃ ግዥ ከናይል ጠቅላላ ንግድ ስራዎች ድርጅት ግዥ ሲፈጸም እና የህንጻ መሳሪያና የኤሌክተሮኒክስ ዕቃ ግዥ ከኤክራም ዘሩ ህንጻና የኤሌክትሮኒክ መደብር ግዥ ሲፈጸም ንብረቱ ከመገዛቱ በፊት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት የተገኘ እና የጽዳት ዕቃዎች፣የህንጻ መሳሪያና የደንብ ልብስ በውስን ጨረታ ግዥ ሲፈጸም ውል ሳይያዝ የተፈጸመ፣
- ጋዞ ወረዳ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ብር 1,031,839.96 ለአስተዳደር ጽ/ቤት አገልግሎት ለሚውለው ተሽከርካሪ ኮድ 4 -06907 የመኪና መለዋወጫ ዕቃ ግዥ በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በቀጥታ የግዥ ዘዴ የተፈጸመ፣
- ሲያደብርና ዋዩ ወረዳ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ብር 1,120,984.11 ለመስኖ ቆላማ አካባቢ ጽ/ቤት አገልግሎት ሸልፍ፣ፋይል መደርደሪያ እና ጠረጴዛ ፣ የመኪና ጎማ፣ መለዋወጫና የጥገና አገልግሎት፣የፕሪንተር ቀለም ግዥ ፣ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃ ግዥ፣ የመጽሀፍት ግዥ እንዲሁም የኤሌክትሮኒክስ ዕቃ ጥገና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም በግልጽ ጨረታ መፈጸም ሲገባው ያለምንም አሳማኝ ምክንያት በቀጥታ የግዥ ዘዴ የተፈጸመ፣
- ወልድያ ከተማ አሰተዳደር ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ብር 5,970,779.88 በከንቲባ ጽ/ቤት ለተለያዩ መምሪያዎችና ተጠሪ ጽ/ቤቶች አገልግሎት የሚውሉ ጠረጴዛዎችና ሸልፎች ግዥ በግልጽ ጨረታ መፈጸም ሲገባው ያለምንም አሳማኝ ምክንያት በቀጥታ የግዥ ዘዴ ተፈጽሞ የተገኘ እና ነሐሴ 19/2014 ዓ.ም በተዘጋጀው የእቅድና ሽልማት ፕሮግራም አገልግሎት የሚውል የወንዶችና የሴቶች የባህል አልባሳት ግዥ ተፈጽሞ በንብረትነት ሞዴሎች ገቢና ወጪ ሳይደረግ የተገኘ መሆኑ፣
- የደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ብር 2,722,368.07 ለጤና ጥበቃ መምሪያ የመኪና ዕቃ ግዥ ሲፈጸም ግዥው ከመፈጸሙ በፊት የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት የሚሉት ከብር 1,000,000.00 በላይ የግዥ አፈፃፀምን ያልተከተለ ግዥዎች የተገኘባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡

ግኝቱ ሊከሰት የቻለውም በአብዛኛው የግዥ መመሪያውን በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ ካለማዋል የተነሣ ሲሆን ገንዘቡ ተገቢዉን ዕቃ (አገልግሎት) ሳያስገኝ እና ፍትሃዊ ውድድርን ሳያስተናግድ ግዥ እየተፈፀመ እንደሆነ በማስገንዘብ ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ

ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በኦዲት ሪፖርቶች ባሳሰብነው መሰረት ብር 382,997.20 (ከ1% ባነሰ) ላይ እርምጃ የተወሰደ ሲሆን ቀሪው ብር 102,703,249.30 ላይ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ግብረ መልስ አልደረሰም፡፡

ይህ የ2016 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረገዉ የግዥ ሂሳብ በ2015 በጀት ዓመት ኦዲት ተደርጎ ከተገኘው ብር 46,599,847.46 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ9 የቀነሰ ሲሆን በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 56,671,454.43 ጨምሮ የተገኘ ሆኗል፡፡ ይህም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የግዥ መመሪያውን በመከተል በኩል ችግሮች እየጨመሩ መምጣታቸውን ያመላክታል፡

የተከፋይ ሂሳብን በተመለከተ፤

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ፤

26. በ2016 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ63 መ/ቤቶች ብር 703,217,996.04 የተከፋይ ዕዳ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ወቅት የፋይናንስ መመሪያውን ተከትሎ ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ ይህ በወቅቱ ያልተከፈለ ወይም ወደ ተጣራ ሀብት መቀየር ያለበት የተከፋይ ሂሳብ ካለፈው ዓመት 120 መ/ቤቶች እና ብር 1,134,090,400.78 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤቶች ቁጥር በ57 የቀነሰ ሲሆን በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 430,872,404.74 ቀነሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም በክልሉ በተፈጠረው የጸጥታ ችግር የኦዲት ሽፋኑ በመቀነሱ የመጣ እንጂ ችግሩ በመሻሻሉ የቀነሱ አለመሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

በወቅቱ ያልተከፈለ ከፍተኛ የተከፋይ ሂሳብ ከሚታይባቸው መ/ቤቶች መካከል የደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 107,201,445.45፣አብክመ መንገድ ቢሮ ብር 74,252,359.00፣ደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 51,260,783.66፣ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 51,126,661.36፣ አብክመ ትምህርት ቢሮ ብር 40,288,511.30፣ቃሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 37,505,883.48፣ደሴ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 36,117,275.48፣አብክመ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ብር 30,527,003.95፣አብክመ ጤና ቢሮ ብር 27,153,587.28፣ ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 21,891,621.87፣ወልድያ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 18,216,029.04፣ደብረ ታቦር ከተማ አስተዳደር

ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 17,834,864.91 እና ተሁለደሬ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 15,511,835.51፣ ከብር 15 ሚሊዩን በላይ የተከፋይ ዕዳ ክምችት በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይሸፍናሉ፡፡

ተከፋይ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመክፈያ ወይም ወደ ተጣራ ሀብት የሚቀየሩበት ጊዜ ስላላቸው በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ብናሳስብም ይህ ዘገባ ጥንቅር እስከተሰራበት ድረስ ተከፋይ ሂሳቡ በምን ሁኔታ እንደሚገኝ አልተገለፀም፡፡

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ፣

27. በ2016 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ10 መ/ቤቶች ብር 32,536,176.52 በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እና መቼ እንደሚከፈል የሚያሳይ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡
ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተከፋይ ሂሣብ በተመለከተ በጥቅሉ ስለተመዘገበ ገንዘቡ ለማንና መቸ እንደሚከፈል ገላጭ ባለመሆኑ በሥራ ላይ ያለውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በመከተል በየጊዜው ክትትል እየተደረገ በየባለቤቱ ተለይቶ መመዝገብ ወይም ለሚመለከተው መከፈል የሌለበት መሆኑን ካልቻለም ወደ ተጣራ ሀብት መቀየር እንዳለበት በሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡
ከዚህ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት ስለመሆኑ ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናቀረበት ድረስ በግብረ መልስ ስላልተገለፀ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አልታወቀም፡፡

የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ኦዲት ውጤት

28. የመንግስት መ/ቤቶች በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እንዲሁም ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች አግባብ ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግበው፤ ክትትል እየተደረገባቸውና በየዓመቱ ቆጠራ እየተከናወነ የንብረት ሂሳብ ለኦዲት ስራ ዝግጁ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉ 202 መ/ቤቶች መካከል በ35(17.33%) መ/ቤቶች የንብረት ሂሳብን ኦዲት ማድረግ የሚያስችል አሰራር ሳይኖር ተገኝቷል፡፡ ንብረትን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ላለመቻሉ ዋና ዋና ምክንያቶች፤

- የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ (የእቃ መቆጣጠሪያ ካርዶች) ባለመቋቋሙ እና ቢቋቋምም ምዝገባ በተሟላ መልኩ ባለመከናወኑ፣
- የንብረት ክፍል ሰራተኞች ሲቀያየሩ የተሟላ ርክክብ የማያደርጉ በመሆኑና ርክክብ ሲደረግም የርክክቡ ቀን ተገልጾ በመዛግብቶችና የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች ላይ መለያ ምልክት አለማድረግና አለመፈራረም፤
- በንብረት ግምጃ ቤት ውስጥ ንብረቶችን ለቆጠራ አመች በሆነ መልኩ በባህሪ፤በእድሜና በአገልግሎት አይነት ለይቶ አለማስቀመጥ፣
- የንብረት ክፍል ሰራተኞች ሲቀያየሩ ማስረከብ የሚገባቸውን ያህል ሳይሆን በቆጠራ የሚገኘውን ብቻ ቆጥሮ ለተተኪዎች የሚያስረክቡ መሆኑ፤
- ንብረት ከመጋዘን ከወጣ በኋላም ቢሆን ሙሉ ለሙሉ ጥቅም ላይ እስኪውል ድረስ ሃብት መሆኑ ታውቆ አለመከታተል፤የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች የየወሩ ከወጪ ቀሪ እየታወቀና እየተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርት አካል እንዲሆኑ አለመደረጉ የሚሉት ዋና ዋና ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም የተጠቀሱትን የንብረት አስተዳደር መሰረታዊ ችግሮች በማረም ሊከሰት የሚችለውን የመንግስት ሃብት ብክነት እንዳይኖር ተገቢው የንብረት አስተዳደር፤አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ በየመ/ቤቱ እንዲተገበርና እንዲጠናከር በየሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡

የኦዲት ግኝቶች የእርምት እርምጃ አወሳሰድ ክትትል በተመለከተ፤

29. የ2016 በጀት ዓመት ሂሳባቸው በመ/ቤታችን በመደበኛ ኦዲት ለተደረጉት 202 መ/ቤቶች በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ አስተያየት መሰረት በ9 መ/ቤቶች የተጠቃለለ የኦዲት ሪፖርት ለየተቋማቱ ከመላካችን በፊት በሰጠነው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት በዚህ ሪፖርት በየግኝት አርዕስቶች የተመለሰ ተብሎ የተመላከተውን የገንዘብ መጠን ሳይጨመር ብር 5,460,633.33 የማስተካከያ እና የማስመለስ እርምጃ ተወስዷል፡፡ ይህ አሰራር ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት እናስገነዝባለን፡፡
30. በ2016 በጀት ዓመት በመደበኛ ኦዲት በተደረጉ 202 መ/ቤቶች የኦዲቱ ሥራ ከመጀመሩ በፊት በተደረገው የክትትል ኦዲት በቀደመው በጀት ዓመት ኦዲት ተደርገው በተገኙ ግኝቶች ላይ በተቋማት ያለው የማሻሻያ እርምት እርምጃ አወሳሰድ ሲጣራ በ12 መ/ቤቶች በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት ይህ የጥንቅር ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ድረስ

የእርምት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፈው ዓመት የኦዲት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

- ገንዳውሃ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በብልጫ እና ድጋሚ የተከፈለ አበል ብር 125,980.23 እና በብልጫ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 29,302.72፣
- ምዕራብ በለሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ኦዲት ማድረግ ያልተቻል መደበኛና ስፖርት ም/ቤት ገቢ ሂሳብ ብር 270,487.12 ፣
- ዳባት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማእከል ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 140,684.51፣አላግባብ የተከፈለ የነዳጅ ዋጋ ብር 4,539.00፣በድጋሜ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 69,309.00፣
- ምዕራብ ደንብያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የግንባታ ስራ ዝርዝር ሳይቀርብለት የተፈጸመ ክፍያ ብር 120,204.55 እና ለኦዲት ስራ ያልቀረበ የስፖርት ም/ቤት ደረሰኝ ብር 83,330.00፣
- ሲያደብር ዋዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ከመቀጠር ከተገኘ ገቢ ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 12,775.00፣
- ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማእከል ለኦዲት ስራ ያልቀረበ የወጪ ሰነድ ብር 113,946.18 ፣ ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 29,749.19፣አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 45,739.80 እና በብልጫ የተከፈለ ክፍያ ብር 4,510.01፣
- ሰሜን ሸዋ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 163,975.15፣
- ሀብሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማእከል ከውል መዘግየት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 3,855.61፣
- ኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ከውል መዘግየት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 10,044.07፣
- ደሴ ከተማ አስተዳር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ከውል መዘግየት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 1,055,880.32፣ያለማስረጃ የተከፈለ ክፍያ ብር 31,017,834.07 እና አላግባብ የተከፈለ ክፍያ ብር 151,610.25፣
- ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ከመቀጠር ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 120,451.63፣

31. በመሆኑም በድምሩ ብር 33,574,208.41 በ12 መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው የቀደመው በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች የተገኙ በመሆኑ በወቅቱ በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ አስተያየት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሜ እያሳሰብን

የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና ተጠያቂነት እንዲጠናከር መ/ቤታችን ከሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ጋር በትብብር የሚሰራውን ሥራ አጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን የእርምት እርምጃ በማይወስዱ እንዲሁም ምላሽ በማይሰጡ አካላት ላይ አስፈላጊው ተጠያቂነት ሊኖር እንደሚገባ እናሳስባለን፡፡

የክልሉ መንግስት የተጠቃለለ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት፤

32. መ/ቤታችን በየበጀት ዓመቱ ተዘግቶ የሚቀርብለትን የክልሉ መንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ (የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ) ኦዲት እያደረገ አስተያየት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡በዚህም መሠረት በ2016 በጀት ዓመት ተጠቃሎ የቀረበለትን የ2014 በጀት ዓመት የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ኦዲት ሥራ በማከናወን ‹‹ከዚህ በስተቀር›› የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በግኝቶቹ ላይም የማስተካከያ እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን የክልሉ ገንዘብ ቢሮ በግብረ መልሱ ገልጿል፡፡ ትኩረት ከሚሹ ግኝቶች መካከል
33. በክልሉ በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ በአጠቃላይ የተገኘው የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 17,931,731,161.64 ሲሆን የተከፋይ ሂሳብ ደግሞ ብር 15,318,051,295.20 እነደሆነ የኦዲቱ ግኝቶች ያሳያል፡፡
34. በቢሮው የተጠቃለለው የሪፖርት አቅራቢ መ/ቤቶች ሁሉም ሂሳቦች መደበኛ ሚዛን ያላቸው ለመሆኑ በናሙና የተመረጡ ሪፖርት አቅራቢዎች (በአንድ ዞን የተመረጡ ከተማ አስተዳደሮች እና ወረዳዎች) የሂሳብ ሪፖርት ሲታይ የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ የመደበኛ በጀት ሂሳብ ላይ በባንክ ያለ ጥሬ ገንዘብ እና የተጣራ ሀብት ሂሳብ በድምሩ ብር 22,927,157.55 የተፈጥሮ ሚዛኑን ሳይጠብቅ ተመዝግቦና ሪፖርት ተደርጎ የተገኘ ቢሆንም በኦዲት ሩፖርቱ መሰረት 1,686,718.03 የተስተካከለ ሲሆን ቀሪው 21, 240,439.52 የተፈጥሮ ሚዛኑን ሳይጠብቅ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ስለተዘጋጀው አመታዊ ሪፖርት ትክክለኛ መረጃ የማይሰጥና በባንክ ያለ ጥሬ ገንዘብ እና የተጣራ ሀብት ሂሳቦች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር በመሆኑ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነት የተዛባና አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡
35. የተጠቃለለ ፈንድ የሀብትና እዳ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተጣራ ሀብት ብር 14,701,533,999.89 የሚያሳይ ሲሆን ነገር ግን ወደ 2015 በጀት ዓመት ሊዛወር

የሚገባው የተጣራ ሀብት ብር 9,461,553,110.21 በመሆኑ በሪፖርት የተላለፈው የተጣራ ሀብት በብር 5,239,980,889.68 በመብለጥ ተላልፎ ተገኝቷል፡፡

ልዩነቱ በክልል ውስጥ የሌለን ሃብት እንዳለ አድርጎ የሚያሳይ እና በሪፖርቱ መሰረት ውሳኔ የሚያስተላልፉ አካላትን ሊያሳስት የሚችል ነው፡፡ ስለሆነም የልዩነቱ ምክንያት በበጀት ዓመቱ የገቢ ተመላሽ ካለ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

36. በመጨረሻም የተከበሩ ፕሬዚዳንት፣ የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤዎች፣ የመንግስት ወጭ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና ሌሎች ኮሚቴዎች፣ የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣ የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሥራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እንዲሁም የመ/ቤቱ ሠራተኞች በዚህ ሪፖርት ለተገኙት ውጤቶች ላሳዩት ታታሪነት እና ላላቸው መልካም ስነ-ምግባር ከፍተኛ ምስጋና እያቀርብኩ ሪፖርቴን በዚሁ አጠቃልላለሁ፡፡

አመስግናለሁ!!

አማረ ብርሃኑ /ዶ/ር /

ዋና ኦዲተር

ህዳር 2017 ዓ.ም

ባህርዳር